# የመጨረሻ ሰይጣን

## ክፍል 9

ከበልጅግ አሊ

አጎቴ ስለአባቴ የሚያውቀውን ሁሉ እንዲነግረኝ በጠየቅሁት ጊዜ ትንሽ አስቦ በሀይል ተነፈሰና አባትህ ብዙ የማይገባ ነገሮች አድርጓል። አንተም ያንን ሳትረዳው የምትቀር አይመስለኝም። ለእኔ እሱ አልሞት ባይ ተጋዳይ ነው። ለሌሎቹ ግን ጨካኝና አውሬ ነው። ባለመማርና እርቀ ባለማሰብ በእልክ ተነሳስቶ ብዙ ሰዎችን መከራ ውስጥ ጥሎአል። ቢሆንም ከተታረቁ በኃላ እንዲ ማድረግ ባልተገባም ነበር።ብሎ ስለ አባቴ ብዙ ነገር አጫወተኝ። ይህ ውይይት በጣም በህይወቴ ከሰማኋቸው ታሪኮች ሁሉ የምወደው ነው።

ከዚህ ውይይት በኋላ ነው ወደ ፖሊስነት ለመግባት ፍላጎቴ የጨመረው። ፖሊስነት እንደተቀጠርኩ ስንዳፋ በሚገኘው ማሰልጠኛ ውሰጥ ትጉህ ስለነበርኩ አስተማሪዎቹ ይደሰቱ ነበር። እኔም ይህንን በመመልከት የበለጠ ጥረት አደርግ ጀመር። በፖለቲካ ትምህርት ወስጥ እሳተፍ ነበር። በወቀትቱ የነበረው የመኢሶን ካድሬ በጣም ይቀርበኝ ነበር። አንዳንድ በተለይም መኢሶን በሚመለከት ፅሁፎች ይሰጠኝ ጀመር። በዛው ለፖለቲካ ያለኝ ዝንባሌ እየጨመረ መጣ።

ወቅቱ በአዲስ አባባ በሊቀመንበር መንግሰቱ ላይ የመግደል ሙከራ የተደረገበት ወቅት ነበርና። አብዮታችሁ ሊቀለበስ ነው በሚል ብዙ ቅስቀሳ ይደረግልን ነበር። ሊቀመንበሩ እንዳገመገሙ የፖሊስ ማሰልጠኛውን ለመጎብኘት እኛ ጋ መጡ። በዚህም ያቀባበል ንግግር እንዳደርግ እኔ ተመረጥኩ ።ምን እንደምናገር ግራ ቢገባኝም በጣም መዘጋጀት እንዳለብኝ አሰብኩ። ይህን አጋጣሚ መቼም እንደማላገኘው ገብቶኛል። ፅፌ ስጨርስ ደጋግሜ አነበብኩት። ሳነብም እንደልሳሳት ጥንቃቄ አደረግሁ። የመኢሶኑ ካድሬ እንዲመለከተው ሰጠሁት።አንዳንድ አነስተኛ መስተካከል ካደረገ በኋላ መለሰልኝ ።

ጓድ መንግስቱ ኃይለ ማርያም

በመጀመሪያ ያልዎትን ወርቅ ጊዜ በመሰዋት ወደኛ በመምጣትዎ ለህግ የበላይነትና ለኛ ለህግ አስከባሪዎች የአልዎትን አመለካከት አጎልቶ ያሳየናል። አብዮታችንን ከውጭም ከውስጥም ለማክሸፍ እንደ ኢሕአፓ ዓይነት የተነሱነብንን ጠላቶቻችንን ወደ ህግ ለማቅረብ የየዕለት ደክምን የማንንልበት ተግባራችን መሆኑን በአንድ ድምፅ ቃል እንገባለን።

ስለፖሊስ ሰራዊት ለእርሶ ለማስረዳት ሙከራም አላደርግም። ይህንን በሚመለከት  የእርሶ እውቀት ከእኔ እንደሚበልጥ ጥርጥር የለኝም።ነገር ግን ከድሮ የፓሊስ ሰራዊት የሚለየን ነገር ቢኖር እኛ ለበዝባዥዎችና፣ ለአቆርቋዦች፣ ለተገንጣዮችና፣ ለአናርኪስቶች የቆምን ሳንሆን አብዮታችንን ለመጠበቅ ዘብ የቆምን ታዛዥዎ ነን። እርሶ የቀሰሉለትን አብዮት እኛ እንሞትለታለን።

ጓድ  መንግስቱ ኃይለ ማርያም

እርሶ የተከሉተን የአብዮት ችግኝ እኛ እናለመልመዋለን።ከእያንዳንዳችን እንደቺሎታችን ይጠበቃል።በተማርነው የምርመራ ዘዴ አካባቢያችንን የሚቆሽሹትን አናርኪስቶች ልናፀዳቸው ይገባል።ሰሞኑን በኢምፔርያልስቶች እና የነርሱ ቅጥረኞች በሆኑት  በእርሶ ላይ የተደረገውን የመግደል ሙከራና ቆራጥ አብዮታውያን እንዴት እንዳከሸፉት  በፅሞና ተከታትለነዋል ።ለእኛ በአብዮቱ ስር ለቆምነውና ለጭቁኑ ነፃነት ለመሞት ለተዘጋጀነው በእርሶ ላይ የተፈፀመውን ደባ በአብየታችን ላይ የተቃጣውን የቅልበሳ ትግል ዝም ብለን ልናልፈው አንፈልግም። የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ነገር ይጠብቃል። ይኸውም በነርዚህ ቅጥረኞች ላይ በአስቸኳይ አብዮታዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው ይገባል። ከዚህ ያነሰ ምንም አይነት ቅጣት በአብዮቱ ጠላቶች ላይ ቢወሰድ ህዝቡ እንደማይቀበለው ከወዲሁ ለማሳወቅ እወዳለሁ።በመጨረሻም በአብዮታችን ላይ የሚፈፀመውን ደባ ሌት ተቀን እንታገላለን።የአብዮቱን ጠላቶች ለማውደም ከጓድ ቀመንበር መንግስቱ ጎን እንቆማለን በማለት ቃል እንገባልን።

ኢትዮጵያ ትቅደም
የኢምፔሪያሊዝም ቅጥረኞች ይወድማሉ።
በአብዮቱ ጠላቶች ላይ አብዮታዊ እርምጃ አሁኑኑ
አሁኑኑ!
አሁኑኑ!

*አሁኑኑ!*

*አመሰግናለሁ ።*

*ይህንን ተናግሬ ስጨርስ መፈክር በማስማበት ግዜ በሊቀመንበር መንግስቱ ላይ ደስታ ይታይባቸው ነበር። እኔም በልቤ ለዚህ ቆራጥ መሪ ብሞትስ ብይ አስብ ነበር። ከስብሰባው በኃላ ተጠርቼ ቀረብኩና ተመሰገንኩ ። ለማሰልጠኛው ጣቢያ አላፊዎች ግን ምን እንደተነገራቸው ባላውቅም በጣም ያከብሩኝ ጀመር። አንዳንዶቹ እንዲያውም ሰላምታ ሊሰጡኝ ይሞክራሉ። የዛ ግዜ ነው በልቤ ውስጥ መፈራትን እየወደደኩ የመጣሁት።በአብዮቱ ውስጥ በመሳተፍ ላገኘው የምችለውን ክብር የተገነዘብኩት።*

*አንድ ቀን ከመኢሶኑ ካድሬ ጋር ስንነጋገር ወደፊት ትምህርቴን ለመቀጠል እንደምፈልግና በተለይም በሽተኛ የሆነውን አጎቴን ለመርዳት እንደምፈልግ ነገርኩት።ለዚሁም እከተማ አካባቢ ካልተመደብኩ አስቸጋሪ እንደሚሆንብኝ አስረዳሁት፡፡ እሱም እንደሚረዳኝ ቃል ገባልኝ ፡፡ ትምህርቱን ስጨርስ ለሃገርህና ለአንተ ወደ ፊት እንድትማር ተብሎ አዲስ አበባ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ተመድበሃል ተብልኩኝ። እንድመደብ ያደረገኝ ካድሬው መሆኑን ገብቶኛል።*

*ከማሰልጠኛው ከመውጣቴ በፊት የመኢሶኑ ካድሬ ወደ ሕዝብ ፅህፈት ቤት ወስዶ ብዙ ሰው አስታዋወቀኝ ከዛም ውስጥ የፓሊስ መኮንን የነበረ ሻለቃ በርሃኑ ከበደ የሚባል የደርግ ፅህፈት ቤት የሚሰራ ፓሊስ መሆኔን ሲያውቅ በጣም ደስ ብሎት እንድደውልልት ስልክ ቁጥሩን ሰጥቶኝ ሄደ። ይህንን ሲያይ የመኢሶን ካድሬው ደስ አላለውም ነበር።እኔም ቀስ ብዬ ማነው ብዬ ጠየቅሁት። ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የፓሊስ ሰራዊት አባል ሲሆን አሁን የደርግ የምርመራ ክፍል አላፊ ነው። አደገኛና ጨካኝ ሰው ስለሆነ አትቅረበው አለኝ። እኔም በወቅቱ ምንም የሚያሳስበኝ ነገር ስላልነበር መልስ ሳልጠው ዝም አልኩት።*

*ከዛም ስለ ወንጀለኛ ምርመር ፣በተለይም ስለፖለቲከኞች ምርመራ፣ በማሰቃየት እውነትን እንዴት ማግኘት እንደሚቻል፣ በሶቬት ህብረት ጥናት አደርጎ ከመጣ በኃላ ይህንን ትምህርቱን በተለምዶ ወፌ ከሚለው ጋር በማገናኘት ብዙ ተመራምሮበታል ይባላል።ግለሰቡ ሰካራምነትና ጨካኝነት አያጣውም።ኢህአፓን በጣም ከማይወዱት ውስጥ አንዱ ነው አለኝ።*

*እኔም በወቅቱ ይህንን ግለሰብ ጋር ህይወቴ ይጣመራል ብዬ ስላላሰብኩ ስለሰውዬው ብዙ ማወቅ አልፈለግሁም ነበር። ሆኖም በአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ የነበረኝ ስራ ከደርግ ፅህፈት ቤት ጋር ብዙ ባያገናኘኝም አንዳንድ ግዜ ተመርማሪ ወደ ደርግ ፅህፈት ቤት የሚወስዱ አንዳንድ መርማሪዎች ሲመጡ ትንሽ መጨዋወት ጀመርኩ። በኃላም ሻለቃ ብርሃኑን እንደማውቅ ነገርኩዋቸው።እነርሱም እንደሚነግሩት ነገሩኝ።ከጥቂት ቀናት በኃላ አንድ የማልጠብቀው ነገር ደረሰ። የፖሊስ ጣቢያው አዛዥ ሻለቃ ጠርተው ደርግ ፅህፈት ቤት ለስራ እንደምፈለግና እንድሄድ ነገሩኝ። በሻለቃው ላይ የፍርሃት ማክበር ይታይባቸው ነበር። ሽማግሌው በአብዮቱ ምንም ቦታ እንደሌላቸው ስላውቅሁ ብዙም አልደነቀኝም። እሳቸውም እኔ የማውቀው ነገር እንዳለ ገብቶቸዋል ። እኔ የጠበቅሁት ግን መርማሪዎቹ መልስ ያመጡልኛል ብዬ እንጂ በእሳቸው በኩል መልስ አገኛለሁ ብዬ አልጠበቅሁም ነበር።የሆነ ሆኖ በደስታ ተቀበልኩት። ዜናው በፖሊስ ጣቢያው ውስጥ በሰፊው ተበተነ። ሁሉም ሰው በጥርጣሬ አክብሮት ይመለከተኝ ገባ።*

*በተባለው ቀን የፖሊስ ልብሴን በደንብ ተኩሼ ለብሼ ወደ ደርግ ፅህፈት ቤት በአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ መኪና ተሰጥቶኝ ከአንድ ፖሊስ ሾፌር ጋር ተያይዘን ሄድን ።መግቢያው በር ላይ ወዴት እንደምንሄድ ተጠየቅን እኔም ሻለቃ ብርሃኑ ጋር እንደሆነ ስነግረው ጠባቂው እንደመደንገጥም እንደመጣደፍም ሲል ለስራ ጉዳይ እንደሆነ ነገርኩት። ብዙም ባያምነኝም ለሌላው ጠባቂ በአይኑ ጠንቀቅ በል የሚል አመለካከት ካየው በኃላ ወደ አንድ ክፍል ገብቶ በሩን ዘጋና ትንሽ ቆይቶ ፈገግ እያለ ተመልሶ መጣ። ከዛም ጓድ ይግረም አሁን ሌላ መኪና መጥቶ ወደ ውስጥ ይወስዶታል የእርሶ መኪና ሊመለስ ይችላል አለኝ። እኔም በምን እመለሳለሁ ለማለት ፈልጌ ነገርግን ማለቱ አስፈላጊ አደለም ሌላ መኪና ከሌለም ስልክ ደውዬ እንዲወስዱኝ አደርጋለሁ ብዬ ፓሊሱን ሾፌር አሰናበትኩት። የጠባቂዎቹ አለቃ በጣም ግዙፍ ሲሆን እንደው ቁጣ ቁጣ ያለውና በጣም ተጠራጣሪ ነው። አይኑ በፍጹም አንድ ቦታ ማረፍ አይችልምም። አንዴ ወደ እኔ ዞር ብሎ እውስጥ ገብቼ እንድቀመጥ ነገረኝ። እኔም ውስጥ ማወቅ የለሌብኝ ሚስጥር ይኖራል፣ በዛውም ቶሎ ይወስዱኛል ብዬ እዚህ ይሻለኛል አልኩት። ወዲያውኑ ፊቱ ተለዋወጠ። እዚህ የምንጠብቅበት ቦታ ነው ለእንግዳ የተዘጋጀው ውስጥ ነው አለኝ። እንደሁኔታው ይህ ሰው ከመንግስቱ በስተቀር ማንም እንደማያዘው ተረዳሁ ለትልልቅ የደርግ ባለስልጣናት እንኳ ከበሬታ እንደሌለው የሚታወቀው የሻለቃ ብርሃኑ እንግዳ ሆኜ እንኳን ክብር ሊሰጠኝ አልፈለገም። በኃላ እንደተረዳሁት ግቢውን የሚጠብቁት በሙሉ ትዕዛዝ የሚቀበሉት ከመንግስቱ ብቻ እንደነበርና የእሱ ቅልቦች እንደሚባሉ ነው። ወዲያው የማውቃቸው መርማሪዎች በመኪና መጥተው አስጠበቅንህ አደለም አንድ አናርኮ አስቸግሮን ነው። ሳንጨርሰው አንመጣም ብለን ቆየን። ብታየው እንደ ድመት ነው ነፍሱ*

ቶሎ አትወጣም ሲሉኝ ደነገጥኩ። ሃሳብ ገባኝ በዚህ ግዜ አንድ እናት ልጆዋን አታለቸች ወይም አንድ አባት ልጁን አጥቶል ወይም አንድ ሴት ባልዋን ወይም አንድ ልጅ አባቱን የሚል ሃሳብ መጣብኝ። ይህ ሁሉ ሃሳብ ደግሞ ወደ ፊት በሚጠብቀኝ ሹመትና ክብር አንፃር ምንም እንዳልሆነና እኔ እራሴ እስካለደረግሁት ድረስ ምንም ችግር እንደሌለው ታሰበኝ። ሰው ገሎ የመጣ ሰው ለመጀመሪያ ግዜ ስላገኘሁ ነው መሰለኝ ፍርሃት ፍርሃት አለኝ። የምንተፍረቴን

- ምን ልሁን ብሎ ነው አናርኮው አልኮቸው?
- አንደኛውእነርሱ እንዲሁ ናቸው አለኝ።በጀግናነት መሞት አለባቸው ስለሚባሉ የማይለፈልፉት የለም። አንዳንዶቹማ መዘመርም ይጀምራሉ። ሞታ የፈለጉ እንደሆን ያስታውቅባቸዋል ።
- ሌላኛው ደግሞ ሞት ከፈለጉ ማን ይከለክላቸዋል አብዮቱ የመጣው ለሁሉም እንደፍላጎቱ ለመስጠት አደለም እንዴ ብሎ አንድ የሚስጠላ ቀጭን ሳቅ ሳቀ።
- የመጀመሪያው መርማሪ በውነቱ የዛሬውማ ትንሽ አስቸጋሪ ነው ወፌ ስናደርገው ምንም ሳይናገር ቆይቶ ከተሰቀለበት ስናወርደውና አፍ ውስጥ የገባውን ኳስ ስናወጣለት የስድቡን ናዳ ጀመረው።ይባስ ብሎ ኢሕአፓ ያቸንፋል ማለት ጀመረ። ገላገልነው እንጂ መጥፎ አናርኮ ነበር።
- መገላገሉ ጥሩ ነው ብላችሁ ብዙ ሳያወጣ? ብላቸው ሁለቱም ባላወዋቂነቴ የሳቁ ይመስል በጣም ከት ብለው ስቀው ከሁሉም አናርኮ ሚስጥር አይገኝም። በተለይ እንደዛሬው አይነቶቹ ምንም ብታደርጋቸው አይናገሩም ስለዚህ መገላገሉ ይሻላል ሲለኝ።
- ሌላኛው ቀበል አድርጎ ማን በእንደዚህ አይነቱ ጉልበት ያጠፋል። ወላድ በድባብ ትሂድ አናርኮ ሞልቶአል አለኝ።
- በል እንግዲህ ሻለቃ ስራ ላይ ስለሆኑ ትንሽ መጠበቅ አለብን እስከዛ እዚህ ትንሽ እንቀማምስ ብለውን ወደ አንድ ትንሽ ክለብ ውስጥ ይዘውኝ ገባን ምግብ ታዘዘና ስንበላ እኔ ስለሁኔታው እያሰብኩ መብላት አቃተኝ።እንደኛው ታዲያ ምነው አትበላም የሻለቃን ግብዣ ካለዚህ አትችለውም አለኝ። እንደምንም ሰአቱ ደርሶ ወደ ሻለቃው ጋር ይዘውኝ ገቡ ።

እንደገባን ሻለቃ ብርሃኑ  ከመቀመጫው ብድግ ብሎ ሰላም አለኝና እነድቀመጥ ጋበዘኝ እነርሱን ስለተመርማሪው ጠያቃቸው። አንደኛው በእጁ ተፈፅማል የሚል ምልክት አሳየው። በጣም ጥሩ ብሎ ካለምንም መደነቅ ቅርብ ወዳለው ኮሜዲኖ ሄዶ ውስኪና ብርጭቆ ይዞ መጣ። ለሁሉም ቀድቶ ለኔም ሊቀዳልኝ ሲል እንደማልጠጣ ነገርኩት። እሱም እሱ ቢሮ ፋንታ ወይም ኮካኮላ  እንደማይገኝ ነግሮኝ ወደ ቁም ነገሩ ቀጠልን።

ባለፈው ግዜ በምረቃችሁ ላይ ያደረግከው ንግግር በጣም ልብ የሚነካና የወቅቱን ችግር እንዴት አድርገን መፍታት እንደምንችል የሚገልፅ ነው። በንግግርህ ሊቀመንበር መንግስቱ ሳይቀሩ በጣም ነው የተነኩት። ከዛም ትምህርትህን ስትጨርስ ወደ ፈለግክበት እንድትመደብ ያደረግነው ለሃገርህ ይበልጥ ታላቅ ተሳትፎ ታደርጋለህ በማለት ነው።  በአምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ሆነህ ከኛ መርማሪዎች ጋር ያደረግከው ትብብር እና ቆራጥነት በጣም አጥጋቢ መሆኑኑን እነርሱም መስክረውልሃል ሲል ሌሎቹ በመስማማት ጭንቅላታቸውን አነቃነቁ ።

አሁንም እንግዲህ አብዮቱ በቅርብ ለማገልገል የምትችልበት ሁኔታ ላይ ነህ ያለኸው።ይህን አብዮት ለማክሸፍ በውስጥም ሆነ በውጭ ጠላቶቻችን ነቅንቀው ተነስተዋል። ኢድዩ ፣ ኢ ኤል ኤፍ ፣ እና ኢሕአፓ ፣በሲ አይ ኤ አስተባባሪነት እንደገና ወደ እዚያ አስከፊ ስርአት እንድንመለስ እየወጉን ነው። በተለይ እንደምታውቀው በዚህ በዋና ከተማችን ቅጥረኞች አብዮቱን እየተፈታተኑት ነው። እነዚህን ቅጥረኞች እንዴት አድርገን እንደምናኮላሻቸው ወደ ፊት እንዳስፈላጊነቱ እናሳውቅሃለን። በተለይ አንተ ፖሊስ ስለሆነክ ብዙ አብዮቱን በተማርከው እንደምትጠቅም አልጠራጠርም።

እኛ እዚህ ውስጥ ያለነው እንደ ስራ ጓዶች ብቻ ሳይሆን እንደ ቤተሰብ ነው የምንተያየው። የአንዳችን ስህተት ሁላችንንም ሊያጠፋ ይችላል። የአንዳችን ውጤት የሁላችንም ውጤት ነው። በቤተሰባችን ውስጥ የአለው ችግር  እንኳ ሳይቀር የጋራችን ነው። እኔ በበኩሌ እናንተን የቤተሰብ ጥቃቅን ችግር ከስራችሁ እንዲያናጥባቸው አልፈልግም ። ሕይወታችሁን የሰጣቸሁለት አብዮት እናንተን መንከባከብ ካቃተው አብዮቱ ፋይዳ አይኖረውም።ታዲያ ችግራችሁን ካላወቅነው በምን ልንረዳችሁ እንችላለን። እኔን ለመንገር ከፈራህ እነርሱ ጓደኞችህ ናቸውና ለእነርሱ ልትነግራቸው ትችላለህ።

እዚህ በምትመጣበት ግዜ የፖሊስ ልብስ እንድትለብስ አያስፈልግም።እሱ ለጥቃት በጣም ያጋልጥሃል።እንግዲህ እዚህ በምትመጣበት ግዜ ከሌሎቹ አንሰህ እንዳትገኝ ለልብስና ለአንዳነድ ነገር ትንሽ ገንዘብ ታዞልሃል። ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ የፖሊስ ልብስ እንድትለብስ አትገደድም። መኪናን በሚመለከት አሁን ለግዜው አስፈላጊ ከሆነ ከኛ ትካፈላለህ። በሚቀጥለው የአናርኮ መኪና ከተገኘ ለሱ ስጡት።

አንተ እንድትከታተልልን የምንፈልገው ከፍተኛ 22 እና ከፍተኛ 4 ነው። እዛ ብዙ አናርኮዎች አሉ። እነርሱን መመንጠር አለብን። በተለይ በዛ አካባቢ የወታደር ካንፖች ስላሉ እዚያ አካባቢ የሚነፍንፉትን ግዜ መስጠት የለብንም። በየቀበሌው ውስጥ የተሰገሰጉትን ደግሞ እንደዚሁ ወደፊት ስለታሰበው እንገልፅልሃለን። በተቻለህ እራስህን ላለማሳወቅ ጣር።ምክንያቱም ለመጠቃት ትጋለጣለህ። አንተ በምትኖርበት ቦታ ምንም እርምጃ አትውሰድ።እዛ አካባቢ ምንም ጉዳይ ብትደርስበት ለኛ አስታውቀን እኛ እርምጃ እንወስዳለን።

በቀበሌው ውስጥ አንዳንድ አብዮተኞች ነን የሚሉ አይጠፉም። እነርሱ ውስጥ ስርጎ ገቦች ይበዙባቸዋል። በአብዮቱ ጥላ ውስጥ ተሰብስበናል ከሚሉትም የታሪክ ሃቅ ነውና ከአብዮቱ ባቡር መውረድ አይቀሬ ነው። እንግዲህ እነዚህን በተመለከተና ሌሎቹን በሞመለከት እነርሱ ያስረዱሃል ብሌ አሰናበተኝ።

ውጭ ከወጣን በኃላ ሌሎቹ መርማሪዎች አብረን ቡና እየጠጣን እንድንጫወት እዛው ክለብ ይዘውን ገባን። ቡናው ከቀረበልን በኃላ አንደኛው መርማሪ እንዲህህ ሲል ጨዋታውን ጀመረ። ሻለቃ የወደዱህ ይመስለኛል። ባይሆን ኖሮ ይህን ያህል ግዜ እራሳቸው ባልሰጡህ ነበር።ይህንን የሳቸውን ባንተ ላይ ያሳደሩብህን እምነት እንደምትወጣው አልጠራጠርም አለኝ። ሌላውም ቀጠል አድርጎ አብዮታችንን መከላከል የምንችለው አብዮታዊ በሆኑ ድርጅቶች ስንሰባሰብ ነው። መቼም እንደምታውቀው አሁን አምስት ድርጅቶች ኢ.ማሌድህን ለማቋቋም ጥረት ላይ ናቸው። እነዚህም

1ኛ. መኢሶን ( መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ)
2ኛ. ማሌሬድ ( ማርክሳዊ ሌሊናዊ ሪቮሉሽናዊ ድርጅት)
3ኛ. ኢጭአት ( የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል)
4ኛ. ወዝ ሊግ
5ኛ. አብዮታዊ ሰደድ።

ናቸው። እንግዲህ እነዚህ የተለያየ ፕሮግራም ቢኖራቸውም አላማቸው አንድ ስለሆነ ህብረት ፈጥረው ሰርቶ አደሩን ፓርቲ ይፈጥራሉ ብለን እናምናለን። እንደውነቱ ከሆነ ግን እስከመጨረሻ አብረውን የማይጓዙ ቢኖሩ ሊደንቀን አይገባም። አብዮት ነውና በየቦታው መንጠብጠብ የማይቀር ታሪካዊ ሃቅ ነው። ወደፊት እንግዲህ ወረቀቶችንና አንዳንድ መፅሄቶችን ስለምንሰጥህ እነርሱን ማንበብ ያስፈልጋል አለኝ ። እኔም እናንተ የዬትኛው ድርጅት አባል ናችሁ ለማለት ፈልጌ አሁን መቸኮል አያስፈልግም ብዬ ተውኩት።

እንደገና አንደኛው እንደምታውቀው ስራችን እራሳችንን ገልጠን ማሳወቅ ስለሌለብን አንዳንድ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን ይኸውም አለባበሳችን የሲቪል ቢሆን በጣም ጥሩ ነው። ምክንያቱ ሰዎች በቶሎ ሊለዩን አይችሉም። መንአልባት አንተ ገና መመረቅህ ስለሆነ አንደንድ የገንዘብ ችግር ሊኖርብህ ስለሚችል ከስራ ማስኬጃችን ላይ ለአንዳን ወጭዎችህ ገንዘብ ይሰጥሃል። ለመጀመሪ የሚሰጥህ ጠቀም ያለ ገንዘብ ስለሆነ ፕሮቶኮልህን እንድትጠብቅ ነው። ጥሩ ጥሩ ልብሶችና ጫማዎች ለመግዛት ሞክር። ሰፈርህ አካባቢ ወደ ሌላ ስር እንደተዘዋወርክና የፖሊስ ልብስ መልበስ እንደማያስፈልግህ ማሰወራት ይኖርብሃል። ከፖሊስ ጣቢያው አዛዥ ትህዛዝ አይደርስህም። ማንኛውንም ጉዳይ ከኛ ጋር ነው የምትሰራው። በፈለግህበት ጊዜ ስራ መግባት ወይም መውጣት ትችላለህ። እኛ ጋ ግን በቀን ሁለቴ መደወል አለብህ ። ይህ ሰለአንተ ደህንነት ማወቅ ስላለንብን ነው። የምትጠራጠረው ወይም የሚከታተልህ ሰው ካለ ወዲያው ለኛ አስታውቀን። ያለህበት ድረስ እኛ እንመጣለን ወይም ኃይል እንልካለን። በተረፈ ወደፊት በሰፊው እንጫወታለን። ብሎኝ አንድ ቢሮ ውስጥ ወስዶ ከሻለቃ የተዘዘውን ለሱ ይሰጠው ብሎ ነገረልኝ። አንድ ወረቀት ላይ እንድፈርም ከተደረገ በኃላ አንድ ሽህ ብር ተሰጠኝ። ገንዘቡን ተቀብዬ ስንወጣ ለምገዛው ነገር ፋክቱር እንደማቀርብ ብነግራቸው ሁለቱም ሳቅ ብለው አንደኛው አብዮቱ በመተማመን ላይ ነው የተመሰረተው ፋክቱር አያስፈልገንም። ቢሆንስ ደግሞ በየቡናቤቱ ፋክቱር ልትጠይቅ ነው እንዴ አለኝ። በመጀመሪያ የገባኝ ለልብስ መግዣ ብቻ መስሎኝ ነበር አሁን ግን ለማናቸውም ወጭ መሆኑን ተረዳሁት።

ከነርሱ ተሰናብቼ መኪና ታዞልኝ ወደ ሰፈር ከተመለስኩ በኃላ በቀጥታ ወደ እኅቴ ቤት ተጓዝኩ። እዛም እኅቴ በጣም ታሞ ስለነበር ጎረቤቶች ተሰብስበው አንዱ ስለጠበል ፣ ሌላው ስለ አዲሱ ሃኪም፣ ሌላው አዲስ ስለተገኘው የሱዳን ጠንቋይ ፣ እያወሩ ለእኅቴ መደሃኒት ይፈልጉ ነበር። እኔም ምንም እኅቴን ብቻውን አግኝቼ ላወራው ብፈልግም የእንግዳው ብዛት ፋታ አልሰጠንም። በሉ ብዬ ተሰናብቼ ከመውጣቴ በፊት ወደ አልጋው ተጠግቼ ሁለት መቶ ብር አስቀምጫ ለማንኛውም ወጭ ይሁንህ ብዬ ተመለስኩ ። ነገር ግን እኅቴ እየደረ በጣም እየታመመ መጣ። ከሚስቱም ጋር ስላልተስማሙ ጥላው ከሄደች ቆይታለች። የእኅቴ በሰፈሩ መኖር ፣ በአካባቢው ህዝብ መከበር ሳስበው እኔ ልሰራው ካሰብኩት ጋር ስለማይመሳሰል በጣም ያስጭንቀን ነበር።

ከደርግ ፅህፈት ቤት አንዳንድ መልክቶች ቢመጡም ሌሎች ፖሊሶች እየተላኩ የኢህአፓ አባሎችንና ተጠርታሪዎችን ያመጧቸውና ወደ ደርግ ፅህፈት ቤት ይወሰዳሉ እንጂ እዚህ ምንም ምርመራ አይደረግላቸውም ነበር ። እየቆየ ግን የስራው ብዛት ከእስረኞችም ያገናኝን ጀመር። የሰፈር ልጆችም ጭምር ይታሰሩ ስለነበር ስሜን መደበቅ የማይቻል ሆነ። ልጁ የት እንደደረሰባቸው የማያውቁ ሰዎች በጠዋት እቤቴ ይመጡና አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ካለ እንድነግራቸው ይጠይቁኝ ነበር። ነገር ግን ፖሊስም ስለነበርኩ በሌላ ነገር ጥርጣሬ ውስጥ አልገቡም።

የአጎቴ በሽታ እየጠነከረ መጥቶ ከፍታኛ ደረጃ ላይ ደረሰ። ዶክተሮቹ ተስፋ ቆርጠው ወደ ቤት ውሰዱት አሉን። እኛም ወስደን እቤት እንዲተኛ አደረግን። አጎቴ ከስንት ስቃይ በኃላ አረፈ። ከፈቀብሩ ስነስርዓት በኃላ ለቅሶ ተቀምጠን ሳለን ከደርግ ፅህፈት ቤት መርማሪዎቹ መጥተው ለማንኛውም ወጭ ብለው አምስት መቶ ብር ሰጥተውኝ ሄዱ። እየተመላለሱም ለቅሶ ደረሱ። ማንኛውም የመጠጥ ወጭ እነርሱ ሸፈኑ። መቼም በዛ ግዜ እንደትልቅ ውለታ ነው የቆጠርኩላቸው።

ለቅሶ አልቆ ስራ ስጀምር እነሱ ጋር በይበልጥ መመላለስ ጀመርኩ ። አሁን አጎቴ የለም። አሁን የምፋራው ነገር የለም። አሁን ምንም የለም። እነርሱ በክፉ ግዜዬ ከአጠገቤ የቆሙ ስለሆኑ ልለያቸው አልፈለግሁም። ደግሞም እራሴን አንድ ትልቅ ቦታ ለማድረስ ከዚህ የተሻለ ምን መንገድ ተገኝቶ ነው።

ወደ እነርሱ በሄድኩ ቁጥር የሚሰጡኝ የወዝ ሊግ ወረቀቶች በመሆኑ የወዝ ሊግ አባል መሆናቸውን ለማወቅ ብዙም ግዜ አልወሰደብኝም። እነርሱም ወደ እዚህ ድርጅት እንድገባ ባይገፋፉኝም አንደ አንድ አባላቸው አርገው ነው የሚያዩኝ። በሌላ በኩል ደግሞ አብሬው የምሰራው የከፍተኛ ሊቀመንበር የሆነ መቶአለቃ ስለ አብየታዊ ሰደድ የሚገልፅ ወረቀት እየሰጠ ሊቀመንበር መግስቱ የሚመሩት ነው በማለት አንዳነበው ይሰጠኝ ነበር። እሱም ቢሆን እንደ ተመልማይ አባል ነበር የሚቆጥረኝ። የሁለቱንም ግንኑነት ሳላቋርጥ ቆየሁ።

አንድ ቀን ሕይወቴን የቀየረ ጉዳይ ተፈፀመ። እንደተለመደው ደርግ ፅህፈት ቤት ሄጄ ሳለ መርማሪዎቹ እስራኛ ለመመርመር ወደ ምርመራ ክፍል ሲሄዱ አገኘኃቸው። ሰላምታ ከተሰጣጠን በኃላ ከፈለግሁ አብሬቻው መምጣት እንደምችል ነገሩኝ። እኔም እሺ ብዬ አብሬቸው ሄድኩ። ወደ አንድ ክፍል ገባን ክፍሉ የአባቴን እሬሳ ያገኘን ለት እንደሸተተኝ አይነት የደም ሽታ ሞልቶታል። ምንአልባት የሞተ ሰው ይኖራል ብዬ ጠረጠርኩ። እንደጠረጠርኩትም ማታ ሲመረምሩት የነበረውን ሰውዬ እዛጥለውት ሄደው ስለነበር በደም ተጨማልቆ ሞቶ አድሮ ነበር። ለኔ ያ እንደትልቅ ነገር ዘገነነኝ። የአባቴን ሞት አስታወሰኝ። ወዲያው ሌሎች እስረኞች መጥተው አውጥተውት ክፍሉን አፅድተው ሄዱ። ሊመረመር የተዘጋጀው ሰውዬ እጆቹ ታስረው እግሮቹ በእጆቹ ውስጥ ከገቡ በኃላ እንጨት መካከሉ ገብቶ በሁለት ወንበሮች ላይ እግሩ ወደ ላይ ጭንቅላቱ ወደ ታች ሆኖ ተሰቅሎአል። እንደገባን ይደበድቡት ጀመር። ሰውዬው ሲጮህ ኳስ የመሰለ ጨርቅ አምጥተው አፉን ጎሰጎሱት። ግርፊያው ሲበዛበት እናገራለሁ ብሎ እጁን አወጣ። የጠየቁትን ሁሉ አዎ አድርጌአለሁ ሲላቸው አወረዱት። እጁንም ፈቱለትና አይኑ እንደተሸፈነ ይጠይቁት ጀመር።እሱ ግን ፊት ያለውን ቀይሮ ግርፉ ስለበዛብኝ እንጂ ምንም አላውቅም ብሎ ካደ። መርማሪዎቹ በጣም ስላናደዳቸው በጣም ይመቱት ጀመር። በዚህ ግዜ አይኑ የተሸፈነበት ጨርቅ ከላዩ ላይ ወደቀ። እስረኛው እኔን ሲያየኝ መሳደብ ጀመረ። አንተ ባንዳ ነህ ለካ እንዲህ የምታደርገው? አለና ጠየቀኝ። ቀስ ብዬ አጠገቡ ተጠግቼ የት እንደሚያውቀኝ ጠየቅሁት። ትምህርት ቤት ነዋ ! ምን የማታውቀኝ ትመስላለህ አለኝ። አሁን ታወቅሁ አለቀለኝ ብዬ አሰብኩ። ልጁ የሚተርፍ ስላልመሰለው ብዙ ይሳደብ ጀመር። ልክ አጠገቡ ስደርስ ምራቁን እፊቴ ላይ ለጎደብኝ። ዓይኔ ለጥፍር መንቀያ የተዘጋጀው ሳንጃ ላይ አረፈ።የአባቴ እሬሳ ፣ የሱ ገዳዮች ፣ ሁሉም ባንድ ግዜ ጭቅላቴን ሞሉት። አይኔ ተጉረጠረጠ ፣ እኔነቴ ተለወጠ። በፍጥነት ሳንጃውን አንስቼ ሆዱ ላይ ሰካሁት ። ደግሜ ደጋግሜ ሰካሁት ። በደከም ድምፅ ለዘመናት እያለ እጄ ላይ ጉልበት እያጣ ተዝለፍልፎ ወደቀ። በሩቅ እንደሚሰማ ድምፅ በጭቆና ማጥ እያለ ወደቀ። ልብሴም እጄም ህይወቴም በደም ተጨማለቀ። ከጎን ከሚገኘው ስንት ቤት ሄጄ እጄን መታጠብ ጀመርኩ። ፍርሃት ነገሰብኝ። ተነስቶ መጥቶ የሚወጋኝ መሰለኝ ። ተንደርድሬ ሄጄ እንደገና ሳንጃውን አንስቼ ያገኘሁበት ቦታ ሁሉ እወጋው ጀመር።ዳግም እንዳይነሳ ፣ ዳግም እንዳያወቀኝ ፣ ዳግም እንዳይመለከተኝ ፣ እደጋግመው ነበር። መርማሪዎቹ መጥተው በቃ ሞቷል ተነስ ብለው ይለምኑኝ ጀመር። ሌላ ሸሚዝና ሱሪ ሰጥተውኝ እነርሱ ጋር እንድቆይ ለመኑኝ እኔ ግን ሁልግዜ ሲከፋኝ እንደማደርገው ብሄራዊ ተያትር ጋር አድርሱኝ አልኩዋቸው። እነርሱም እዛ ጋ አደረሱኝ ። ቀስ ብዬ ወደ ሰንጋተራ መጓዝ ጀመርኩ። በመንገድ ላይ ብዙ ሃሳቦች መጡብኝ።

ይቀጥላል